# መግ ቢ ያ

የመሰረተ እምነት (ትምህርት) ዓላማ በሰሜን አሜሪካ ላሉ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን እምነት ተከታዮች ስለ ርትዕት ሐይማኖታቸው መሰረታዊ የቤተክርስቲያኒቱ አስተምህሮ (ዶግማ ቀኖና እና ትውፊት) ግንዛቤ እንዲይዙ ለማድረግ በአጭሩ የተዘጋጀ ነው፡፡ ይህ ፅሑፍ ለ25ኛ ዕመታዊ የምስረታ በአል ለምናቀርበው አውደ ርዕይ ከተለያዩ ቅዱሳት መጽሐፍት እና አባቶችን ጠይቀን የቀረበ ጽሑፍ ነው፡፡

# ዶግማ

## ***<u>የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን ዶግማ (እምነት) ባጭር ትንታኔ</u>***

***<u>ዶግማ</u>***:- ቃሉ ከግሪክ የወጣ ሲሆን እምነት እውነት ተብሎ የሚታመን የሚታየውን እና የማይታየውን የፈጠረ አምላክን ማመን ነው::

***<u>ዶግማ</u>*** :- ማለት የአንዲት እምነት መሠረት (መመሪያ) ማለት ነው ይህም ማለት ፣ የእምነቱ (የምትከተለው እምነት ትንታኔ) ማለት ነዉ ።

ስለዚህ ዶግማ፣ የማይቀየር የማይለወጥ የማይሻሻል የእምነት መሠረት ነው። ዶግማ ተለወጠ(ተሻሻለ) ማለት እምነት ተለወጠ ማለት ።ስለዚህ ቤተክርስቲያናችን እንደሚከተለው ታምናለች እግዚአብሔር-ሁሉን የፈጠረ በአንድነት እና በሦስትነት የሚመለክ ሕያው አምላክ ነዉ ይህም ማለት:-

### ***<u>አምስቱ አእማደ ምስጢራት</u>***

#### ***<u>ምስጢረ ሥላሴ</u>***

የእግዚአብሔር አንድነት እና ሦስትነትን የሚገልፅ ሲሆን እግዚአብሔር አንድ ሲሆን ሦስት ሦስት ሲሆን አንድ እንደሆነ ያስረዳል ። ከላይ የቤተክርስቲያን አስተምህሮ በጥቅሉ እንደተፃፈ ሆኖ ወደ ውስጥ ጠልቀን ስናብራራው መፅሐፍ ቅዱስ እንደሚከተለው ያስረዳናል በብሉይ ኪዳን እግዚአብሔር በስም በአካል እና በግብር ሦስት ሲሆን በመለኮት በባህሪ በአገዛዝ ግን አንድ እንደሆነ አስረጅ ጥቅስ የሚሆነን ዘፍ. 1:26 "እግዚአብሔርም አለ ሰውን በመልካችን እንደ ምሣሌያችን እንፍጠር ሲል : እግዚአብሔርም አለ ብሎ አንድነቱን ሰውን በመልካችን ብሎ ብዛትን (ከአንድ በላይ መሆኑን) ያስረዳል ወደ ሀዲስ ኪዳንም ስንመጣ የማቴ.ወ. 28:19 "ሂዱና አህዛብን በአብ በወልድ በመንፈስ ቅዱስ ስም እያጠመቃችሁ ደቀ መዛሙርት አድርጋቸው" ሲል ሦስትነቱን በግልፅ ያስረዳናል በመለኮት በባህሪይ እና በአገዛዝ አንድ እንደሆነ በዮሐ. ወ. 10:30

ለፊሊጶስ "እኔና አብ አንድ ነን" እኔ በአብ አብም በእኔ እንዳል እመኑ ሲል ከባህሪ አባቱ አብ ከባህሪ ህይወቱ መንፈስ ቅዱስ ጋር አንድ እንደሆነ ያስረዳናል ስለዚህ እግዚአብሔር አንድም ሦስትም መሆኑን ቤተክርስቲያን ታምናለች።

## <u>ምስጢረ ስጋዌ</u>

የአምላክ ሰው የመሆን ምስጢር ማለት ሲሆን እግዚአብሔር ወልድ ሰውን ለማዳን በሥጋ ማርያም (የእመቤታችንን ሥጋ ተዋህዶ) መገለጡን የሚያስረዳ ነው እግዚአብሔር ወልድ ሰው ሆነ ስንል አምላክነቱ የጎደለበት (የቀረበት) አይደለም የነበረው ያለው እና የሚኖረው ቃል ሥጋ ሆነ እንጂ በባህሪው ሞት ህልፈት የማይስማማው አምላክ ሰውን ለማዳን ደካማውን ሥጋ ተዋህዶ መገለጡን የሚያስረዳ ነው ዮሐ. ወን. ም. 1:3 ስለዚህ ክርስቶስ አንድ አካል አንድ ባህሪ መሆኑን አምነን በመለኮቱ እግዚአብሔር በሥጋ ደግሞ የአዳም ልጅ (የማርያም ልጅ) እንደሆነ እንመሰክራለን ወልድ

ከአብ ከመንፈስ ቅዱስ በመለኮቱ ሳይለይ የእኛን ሥጋ ተዋህዷልና።

## <u>ምስጢረ ጥምቀት</u>

የቃሉ ትርጉም መነከር መዘፈቅ ውሃ ውስጥ ገብቶ መውጣት ሲሆን ጥምቀት ከእግዚአብሔር የመንፈስ ልደትን የምናገኝበት ምስጢር ነው ዮሐ ወ 3:3-6 ሰው ሁሉ ሁለተኛ(ዳግም) ከውሃ እና ከመንፈስ በጥምቀት ካልተወለደ በስተቀር ወደ እግዚአብሔር መንግስት ይገባ ዘንድ አይችልም ከሥጋ የተወለደ ሥጋ ከመንፈስ የተወለደ መንፈስ ነውና ጥምቀት አንዲት ስለሆነች አትደገምም አትከለስም የምትፈፀመውም በአንዲት ሐይማኖት(ቤተክርስቲያን) ውስጥ ነው ። ጥምቀት የክርስትና መግቢያ በር ስትሆን ወንዶች በ40 ሴቶች በ 80 ቀናቸው የሚፈፅሙት (የሚጠቀሙበት) ምስጢር ናት የምንጠቀምውም በአብ በወልድ በመንፈስ ቅዱስ ሥም ነው ማቴ.28:19

## <u>ምስጢረ ቁርባን</u>

ሙታን ወቁርባን በቅዳሴ ግዜ ቀሳውስት የሚያቀርቡት ህብስት ተለውጦ (ሥጋ) ህብስተ መለኮት (መለኮት የተዋሀደው) የሚያቀርበውም ፅዋ ተለውጦ ደመ መለኮት (መለኮት የተዋሀድው) የህይወት ወይም የነፍስ ምግብ ነው ዮሐ.6:35" ሥጋዬን የበላ ደሜን የጠጣ የዘላለም ሕይወት አለው" ክርስቲያኖች ከአምላካችን ጋር አንድ የምንሆንበት ምስጢር ነው ይህ ቁርባን ምሳሌ ወይም መታሰቢያ ሳይሆን አማናዊ ቁርባን ነው ሥጋዬን የሚበላ ደሜን የሚጠጣ አለ እንጂ ምሳሌያዊ(መታሰቢያ) ነው አላለም ስለዚህ ምስጢረ ቁርባን መዳናችን የተፈፀመበት የምሥጢራት ሁሉ ዘውድ (ምሥጢረ ምሥጢራት) ነው በፀሎተ ሐሙስ በተግባር ፈፅሞ ያሳየን ሲሆን እኛም የምንሳተፈው በዚሁ ዕለት የተፈፀመውን አማናዊ ምስጢር ነው ማቴ.26:28

## ምስጢረ ትንሣኤ

ትንሣኤ ሙታን ማለት ተለያይተው በተለያየ ስፍራ ይኖሩ የነበሩ ነፍስ እና ሥጋን እንደገና ተዋህደው መነሳትና ከሞት በኻላ በነፍስና በሥጋ ሕይወት ማግኘት ማለት ነው የትንሣኤያችን በኩር አምላካችን እና ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ነው እርሱ ሞትን ድል አድርጎ እንደተነሳ በእርሱ ያመንን እና የተጠመቅን ክርቲያኖች ሁሉ እነሣለን ትንሣኤ ያስፈለገበት ምክንያት ሰው የተፈጠረው ዘላለማዊ ህይወት ኖሮት እንዲኖር ነበር(ዘላለማዊ ሆኖ እንዲኖር1ኛ ተስሎ 13:16 "ስለዚህ ሞት በአንድ ሰው (አዳም ) ምክንያት ወደ ዓለም ገባ (መጣ) በክርስቶስ ደግሞ ትንሣኤ ሆናል በትንሳኤ ሙታን መልካም ያደረጉ ለሕይወት ትንሳኤ ወይም ሊፈረድላቸው ክፉ ያደረጉ ደግሞ ለከፋት ትንሳኤ ሊፈረድባቸው ይነሣሉ ዮሐ.5:28 ስለዚህ ቤተክርስቲያን በትንሳኤ ሙታን ሰው ሁሉ እንደሚነሳ ታምናለች ። ምስጢር የተባሉት ለሚያምኑት ሳይሆን ለማያምኑት ነው በአፈፃፀም ደግሞ አገልግሎት የማይታይ ፀጋ ስለምናገኝባቸው ነው።

በመ

- በአካል በሥም በውስጣዊ ግብር ሶስት ሲሆን ይህን ሦስት የሚለውን ቃል ሥላሴ ይገልጠዋል::
- በአገዛዝ በመፍጠር በስልጣን እና በመሳሰሉት አንድ አምላክ ነዉ ይህን ደግሞ ፈጣሪ እግዚአብሔር አምላክ እና የመሳሰሉት ስሞቹ ይገልጡታል::
- እግዚአብሔር አብ (አብ) ቅድመ አለም የነበረ ነዉ ያልነበረበት ጊዜ የለም የወልድ የባህሪ አባት መንፈስ ቅዱስን ያሰረፀ ሁሉን የፈጠረ ህያው አምላክ የወልድ እና የመንፈስ ቅዱስ ልባቸው ነው::
- እግዚአብሔር ወልድ (ወልድ)ቅድመ ዓለም የነበረ ነው ያልነበረበት ጊዜ የለም ቅድመ ዓለም ያለ እናት ከአብ ድህረ ዓለም ያለ አባት ከቅድስት እመቤታችን ድንግል ማርያም የተወለደ ነው::

- የአብ የባህሪ ልጅ ሁሉን የፈጠረ( ያስገኘ) ሕያው አምላክ ነው የአብ እና የመንፈስ ቅዱስ ቃላቸው ነው::

- እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ (መንፈስ ቅዱስ) ቅድመ ዓለም የነበረ ያልነበረበት ጊዜ የሌለ ከአብ የሰረፀ አምላክ ነው የአብ እና የወልድ እስትንፋሳቸው (ህይወታቸው) ነው::

- መድሀኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በፍጹም ተዋህዶ ሰው የሆነ አምላክ ነው የቀጥተኛዋ ሃይማኖት መስራች የቤተክርስቲያን ራስ ዓለምን የፈጠረ ዓለምን ያዳነ በመጨረሻም የፈጠረውን ዓለም ለማሳለፍ ዳግም የሚመጣ በፃድቃን እና በሃጥአን የሚፈርድ እርሱ ራሱ ነው ። በከዊን ስሙ (በመሆን ስሙ) ቃል በግብር ስሙ ወልድ በስጋዊ ስሙ ክርስቶስ አማኑኤል ይባላል ስለሆነም ስለ ሃጢያታችን ራሱን ቤዛ አድርጎ ህይወት የሆነን እርሱ ነው::

- እመቤታችን ድንግል ማርያም አምላክን በድንግልና ፀንሳ በድንግልና ወለደችው ከመውለድው በፊት በወለደችውም ጊዜ ከወለደችውም በኋላ ድንግል ናት የአምላክ እናት ናት ከሰው ዘር ሁሉ የአዳም ሐጢያት ያልተላለፈባት እርሳ ብቻ ናት በቅዱሳን እና በአምላክ መካከል የምትገኝ ስለሆነች ቅድስት ቅዱሳን የሚል ስያሜ ተሰጥታታል ከተቀደሱት ቅዱሳን ይልቅ የተቀደሰች ልዩ ማለት ነች::

- ተዋህዶ መለኮት እና ትስብዕት (ሰው (ሰውነት)በተዋህዶ ጊዜ ያለመለዋወጥ ያለመቀላቀል ያለመለያየት ያለመጠፋፋት አንድ ሆነዋል(ተዋህደዋል)::

- ትንሳኤ ሙታን ሰው ሁሉ በትንሳኤ ሙታን ስጋ እና ነፍሱ ተዋህደው ይነሳና በልዩ (መንፈሳዊ አካል) በነፍሱ ዘላለማዊ ፍርዱን ተቀብሎ ይኖራል በመሆኑም የስው ነፍስ ተፈርዶላት ወይም ተፈርዶበት ዘለዓለም የምትኖር ህያዊት ናት።

- የአዳም ሐጢያት ፣ከእመቤታችን ከድንግል ማርያም በስተቀር በሰው ዘር ሁሉ ላይ ተላልፋል::

- ቅዱሳን፣ቅድሳን መልእክት እና ቅዱሳን ሰዎች በተሰጣቸው ክብር እና ስልጣን ምልጃን(ማማለድን) ያከናውናሉ የፀጋ (የአክብሮት) ስግደትም ይሰገድላቸዋል::

- ጽድቅ እና ድህነት፣ መጽደቅ እና መዳን የሚቻለው በእምነት እና በመልካም ስራ(ምግባር) በሁለቱ ጣምራነት ነው እምነት ከምግባር ምግባርም ከእምነት ተለይቶ ለድህነት እያበቁም አንዱ ከሌላው ከተለየ ነፍስ የሌለው ስጋ ይሆናል::

- ቅዱሳት መፃህፍት: የቤተክርትያናችን የዶግማ መሰረት መፅሐፍ ቅዱስ ሲሆን በእግዚአብሔር መንፈስ የተፃፉን ቅዱሳት መፃህፍት እና መፅሐፍ ቅዱሳዊ መሰረት ያላቸውን ገድላትን እና ተአምራትን እንዲሁም ድርሳናትን ትቀበላለች::

- ቤተክርስቲያን: አንዲት ቅድስት ዓለም ዓቀፋዊት እና ሐዋርያዊት ናት::

- ***<u>ጥምቀት:</u>*** ከእግዚአብሔር በመንፈስ ዳግም ልደትን እና የሐጥያት ስርየትን የምታሰጥ ጥምቀት አንዲት ናት::

- ሰባቱ የቤተክርስቲያን ምስጢራት ምዕመናን በሰባቱ የቤተክርስቲያን ምስጢራት አማካኝነት የማይታዩ በእምነት የምናያቸውን ልዩ ልዩ ክብርን ያገኛሉ። እነዚህም ምስጢራት ምስጢረ ክህነት፣ጥምቀት፣ሜሮን፣ቁርባን፣ተክሊል ፣ንስሐ እና ቀንዲል እነዚህ በእግዚአብሔር እና በፍጡር መካከል የተዘረጉ የፀጋ እና የክብር መተላለፊያዎች ሲሆኑ በእነዚህ ካልሆነ በስተቀር ሰው ከአምላኩ ጋር እድል ፈንታ የለውም::

- ቁርባን ከካህኑ ፀሎት ከቅዳሴው ስርአት ፍፃሜ በሓላ አማናዊው (ትክክለኛው) የክርስቶስ ስጋ እና ደም እንጂ መታሰቢያ አይደለም::

- ክህነት የክህነት ደረጃዎች ሦስት ናቸው እነዚህም ከዝቅተኛው ወደ ከፍተኛ ስንቆጥር ድቁና፣ቅስና እና የተባሉት ሲሆኑ ከሦስቱ ሁለቱ ድቁና እና ቅስና ለባለትዳር ሊሰጡ ይችላሉ ኤጲስ ቆጶስነት ግን ለድንግላዊ የሚሰጥ ስልጣን ነው የሐይማኖት ጉባኤያት በኒቅያ በኤፌሶን እና በቁስጥንጥንያ ሶስቱ ዓለም አቀፍ ጉባኤያት ስብሰባዎች በመንፈስ ቅዱስ መሪነት የተከናወኑ ስለሆኑ ቤተክርስትያናችን የተቀደሱ ነው ብላ ትቀበላቸዋለች::

- በመንፈሳዊ እስተዳደር የማይታየው በእምነት የምናየው መንፈሳዊ የቤተክርስቲያን መሪ (ራስ) ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሲሆን ምድራዊ የቤተክርስቲያን መሪ እና የክርስቶስ ተወካይ የቅዱስ ሲኖዶስ ጉባኤ (የሊቃነ ጳጳሳት ጉባኤ) ነው ቤተክርስቲያናን የሚወክለው እና የሚመራው በቤተክርስቲያንና የዶግማ ስርዓት እና የተለያዩ ጉዳዮች ስልጣን ያለው ይህ የቅዱስ ሲኖዶስ ጉባኤ ብቻ ነው። ቤተክርስቲያን የምትቀበላቸው ጉባኤያት በዝርዝር

- ንጉስ ቆስጠንጢኖስ በ------- ዓ.ም ማንኛውም ሰው ያመነበትን እምነት እንዲከተል ነፃነት ከሰጠ በሁዋላ የተለያዩ የስህተት ትምህርቶች መምጣት ጀመሩ::

፩. **<u>አርዩስ</u>**: ወልድ ፍጡር እንጂ አምላክ አይደለም በማለት ያስተማረው በ 325 ዓ.ም በኒቂያ ጉባኤ 318ቱ ሊቃውንት አርዮስን የለዩበት እና ጸሎተ ሐይማኖት የተደረሰበት(የተዘጋጀበት) የተፈጠረ ያይደለ የተወለደ(በመለኮቱ ከአብ ጋር የሚተካከል) -እውነት ነው ያሉትን ሁሉ በመግለፅ ስህተት የሆነውን እየለዩ እስረድተዋል ሐዋ:፲፣፱ ኢየሱስ ጌታ እንደሆነ ብትመስክር ትድናለህ...

፪. ሀ.***<u>መቅዶንዮስ</u>***.- ከአርዮስ ቀጥሎ በክህደት ትምህርቱ ቤተክርስቲያን ሊያውክ የነበረው መቅዶንዮስ የተባለ መናፍቅ ነው:: ይህ መናፍቅ ከቅድስት ሥላሴ ሶስተኛው አካል መንፈስ ቅዱስ ሕጸጽ (ፍጡር) ነው አካል የለውም ብሎ የክህደት ትምህርቱን ባስተማረ ጊዜ በ381 ዓ.ም በቁስጥንጥያ 150 የሚያህሉ ሊቃውንት ታድመው የመንፈስ ቅዱስን የባህርይ አምላክነት ከአብ ከወልድ ጋር በአንድነት የሚሰለስ የሚቀደስ መሆኑን መጽሐፍ ቅዱስን በመጥቀስ አስረድተውታል ከስህተት ትምህርቱ አልመለስ ስላለ ተወግዟል::

- ፫.***ንስጥሮስ***:ሁለት ባህሪ(ድንግል የወለደችው ክርስቶስን እንጂ አምላክን አይደለም ወልድን በመለኮቱ ይቀበልና ከእመቤታችን መወለዱን አያምንም(ወላዲተ አምላክ አትባልም ይል ነበር .እመቤታችን ግን እምቅድመ አለም የነበረውን ያለውን የሚኖረውን ነው የወለደችው በማለት በ431 ዓ.ም በኤፌሶን ጉባኤ ወደ 200 ሊቃነ ጳጳሳት በመሰባሰብ የንስጥሮስን ትምህርት አስተካክለዋል ቤተክርስቲያናችን በነዚህ በሦስቱ ዓለም አቀፍ ጉባኤዎች ሐዋርያቶች የወሰኑትን ትቀበላለች።

# ***ቀኖና፡***

***ቀኖና***፡_ ቃሉ የግሪክ ሲሆን መስፈሪያ መለኪያ መመጠኛ ማለት ነው። እንደ ሸምበቆ ያለ ርዝመትን ለመለካት የሚጠቀሙበት እንጨት ማለት ነው። በቤተክርስቲያን አባቶቻችን ጳጳሳት በቅዱስ ሲኖዶስ ተሰብስበው ለአገልግሎት(ለሥርዓት)የሚያስተላልፉት ዉሳኔ ቀኖና ይባላል። ቀኖና በቅዱስ ሲኖዶስ ሊለወጥወይም ሊሻሻል ይችላል።

ቀኖና የቤተክርስቲያንን መሰረተ እምነት(ዶግማ)ለመፈጸም የምንመራበት፣ የምንለካበት፣ ሲሆን ቀኖናን በተግባር የምናውለው ደግሞ በሥርዓት ቤተክርስቲያን ነው፡

***ሥርዓት***፡- (ሠርዐ) ከሚለው የግዕዝ ግስ የወጣ ሲሆን ትርጉሙ ደንብ፣ አሰራር፣ መርሓ ግብር ማለት ነው። ስለዚህ ሥርዓተ ቤተክርስቲያን ስንል የቤትክርስቲያን ህግ፣ የቤተክርስቲያን ቀኖና፣ አሰራር፣ ወይም ደንብ ማለታችን ነው።

**<u>ቤተክርስቲያን</u>፡-** ማለት ሦሥት ትርጉም ያለው በዘርፍና በባለቤትነት የተቀመጠ ሥም ነው። ይኸውም አንደኛው ትርጉም የቤተክርስቲያን ሕንጻው (ቤት)፣ ሁለተኛው ትርጉም የክርስቲያን አንድነት ጉባዔ፣ እንዲሁም ሦሥተኛው ትርጉም የክርስቲያን ሰውነት ማለት ነው። ሥርዓተ ቤተክርስቲያን ስንል ለዚሁ ከላየ ለዘረዘርናቸው ሦሥት አካላትን ለመምራት የተሰራ ህግ ማለታችን ነው። በመሆኑም አንድ ምዕመን ወይም ክርስቲያን ቢያንስ ዋና ዋናዎቹን የቤተክርስቲያን ሥርዓት መማርና ማወቅ ይጠበቅበታል። በዚህም መሰረት ምዕመናን ግደታቸውን በመረዳት መብራቱን፣ ማዕጠንቱን፣ ሥዕለቱን፣ መባውን፣ የሰበካ ጉባዔ አስተዋጽዖውን፣ አስራቱን፣ በኩራቱን፣ ቀዳሚያቱን ለቤተክርስቲያን በማምጣት ቤተክርስቲያንንና የቤተክርስቲያን(መንፈሳዊ)አገልግሎት የሚሰጥባቸውን ቤቶች መስራት፣ መጻህፍትን፣ አልባሳትን፣ ንዋያት ቅድሳትንና ይህን የመሳሰሉትን ለቤተክርስቲያን በመስጠት ግዴታቸውን መፈጸም ያስችላቸዋል።

መብታቸውንም በመጠቀም ትምህርተ ወንጌልን ማግኘት፣ ሲወልዱ ክርስትና ማስነሳት፣ ሜሮን ማስቀባት፣ ቁርባን ማግኘት፣ በኃጢዓት ሲወድቁ ንስሃ ሲገቡ ከካህኑ ቀኖና ጸሎተ ፍትሐት ማግኘት፣ ሲታመሙ ቀንዲል መቀባት፣ ጋብቻቸውን ሲፈጽሙ የቃልኪዳንና የተክሊል ሥርዓተ ጸሎት ማግኘት፣ ሲሞቱ መፍታትና ይህን የመሳሰሉ አያሌ ጸጋዎችን ከቤተክርስቲያን በማግኘት እምነታቸዉን በተግባር ይተረጉሙታል።

በቤተክርስቲያን ቀኖና የሚለውን ቃል ስንጠቀም የመጻሕፍቷን ዝርዝር የሥርዓተ አምልኮቷን አፈጻጸም የምሥጢራተ ቤተክርስቲያን አፈጻጸም የአንድን ክርስቲያን ሥነምግባር ምን መምሰል እንዳለበት በዝርዝር ለመግለጽ ነበር። ነገር ግን በየጊዜው ይከሰቱ የነበሩ ከእምነት ከምግባር የወጡ ሰዎች ምዕመናንን ግራ እንዳያጋቡ ከእምነት እንዳያስክዱ ለማድረግ ቀኖና ይወጣ ጀመር። እንደ ችግሩ መጠን የሚወጡት ቀኖናት ዳርቻቸው ከአጥቢያ እስከ ዓለም አቀፍ ይዘት ነበረው። የቀኖና ቤተክርስቲያን ዋና ዓላማ ሰዎችን በሥርዓት እንዲጓዙ በማድረግ ዘላለማዊ ሕይወትን እንዲያገኙ ማድረግ ነው። የቤተክርስቲያን ቀኖናት የተሰጡት በሐዋሪያት

ነው። በእነርሱ ወንበር የተቀመጡት ሊቃነ ጳጳሳትም በቅዱስ ሲኖዶስ አማካኝነት ጊዜውን የዋጀ ቀኖና ሰርተዋል ይሰራሉ።

# *የቀኖና ምንጮች*

## *ሀ. የሐዋርያት ሲኖዶስ*

ቅዱሳን ሐዋሪያት በመንፈስ ቅዱስ መሪነት እየተሰበሰቡ የደነገጓቸው የሥርዓት መጻሕፍት ሁለት ሲሆኑ ከሰማኒያ አሃዱ መጽሐፍ ቅዱስ የሚካተቱ ናቸው። እነርሱም መጽሐፈ ዲድስቅሊያ እና መጽሐፈ ሲኖዶሳት ናቸው። መጽሐፈ ሲኖዶስ የሚባለው ትዕዛዝ(ረስጡብ)፣ ግጽው(ረስጠጅ)፣ አብጥሊስ(ረስጣ ወይም ረስጥአ)፣ እና ሥርዓተ ጽዮን(ዓይን) የሚባሉ አራት ክፍል ያለው ሲሆን በውስጡ ስለ ሥርዓተ ቅዳሴ፣ ስለ አገልጋዮች ማዕረጋት ቀኖና ይናገራል። መጽሐፈ ዲድስቅሊያ ደግሞ ስለ ክርስቲያናዊ ሥነምግባር እና ሥርዓት አምልኮ በዝርዝር ይናገራል።

## ለ ዓለም አቀፍ ጉባዓያት

ዓለም አቀፍ ጉባዓያት የሚባሉት ከሁሉም አቢያተ ክርስቲያን የመጡ የቤተክርስቲያን ተወካዮች ሲኖሩበት የጉባዔው መነጋገሪያ አጀንዳ ዓለም አቀፋዊ ሲሆን እና የሚወሰነው ውሳኔም በሁሉም አቢያተ ክርስቲያን ተፈጻሚ ሲሆን ነው። በዚህም መሰረት የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን ሦሥት ዓለም አቀፋዊያን ጉባዔያት በእነዚህ የተደነገጉ ቀኖናትን ትቀበላለች።

**እነዚህ ጉባዔያት:-**

ሀ) በ፫፻፳፭ ዓ ም ፫፻፲፰ቱ ሊቃውንተ ቤተክርስቲያን የተገኙበት አሪዮስን ለማውገዝ በኒቂያ የተካሄደው ጉባዔ ኒቂያን በዚያም የተላለፈውን ቀኖና(ጸሎተ ሃይማኖትና ሥርዓትን በተመለከተ የተላለፈውን ባለ፳ አንቀጽ ውሳኔ አስተላልፈዋል።

እነዚህም

ስለመናፍቃን ጥምቀት፣ ስለ ትንሳዔ በዓል አከባበር፣ ስለ ድንግልና ኑሮ፣ ስለ መባጥዮስ የአሳዩት ኤጵስ ቆጶሳት፣ ስለ ጳውሎስ ሳምሳጢን (ጳውሎስ ሳምሳጢን ብሳምሳታ ከሀብታም ወገን የተወለደ መናፍቅ ጳጳስ ነበር) በምስጢረ ሥላሴ ላይ <ቃል ከሥጋዌ በፊት በአካላዊነት አልነበረም በአብ አካል ውስጥ ያለው ዝርው ቃል(ኃይል)ነበር አለ>።

በምሥጢረ ሥጋዌ ላይም <ድንግል ማርያም የወለደችው ኢየሱስ ዕሩቅ ብእሲ ነው> በማለት የሳተ ያሳተ መናፍቅ ነበር። በጳውሎስ ሳምሳጢን ትምህርት አምነው የተጠመቁ ቢኖሩ ጥምቀታቸው በአብ በወልድ በመንፈስ ቅዱስ ሥም ስላልተፈጸመ እንዳልተጠመቁ ተቆጥሮ ዳግመኛ እንዲጠመቁ < በጳውሎስ ሳምሳጢን የተጠመቀ ቢኖር ዳግመኛ ያጥምቁት> ሲል ጉባዔው ውሳኔ አስተላልፏል። ስለ ክርስትና እናትና አባት (ኒቂያ ፳፱) በቤተክርስቲያን ካህናትና ምዕመናን በተወሰነላቸው ቦታ እንዲቆሙ ዲያቆናት ማስተናበር እንዳለባቸው(ኒቂያ ፳፩)

***ለ) ጉባኤ ቁስጥንጥንያ*** (በ፫፻፹፩ ዓ።ም። የተካሔደ) እና ጉባኤ ኤፌሶን (በ፬፻፴፩ ዓ።ም። የተካሔደ) ናቸው። በእነዚኽ ዓለም አቀፍ ጉባኤያት ብዙ ቀኖናዎች ተደንግገዋል። ለምሳሌ በጉባኤ ኒቅያ ከተወሰኑት ቀኖናት የትንሣኤ በዓል እሑድ መከበር እንዳለበት፣ ስለ አርዮስ ጉዳይ፣ ስለ መጻሕፍት ጉዳይ፣ ስለ አራቱ መንበረ ፓትሪያሪኮች ይገኙባቸዋል።

## ሐ) ብሔራውያን ጉባኤያት

ከዓለማቀፋውያን ጉባኤያት በተጨማሪ በየአካባቢው ጉባኤያት ሊደረጉ ይችላሉ። ለምሳሌ በቅዱስ ያሬድ ዜማ ላይ የግብጽ ቤተ ክርስቲያን ጉዳይዋ አይደለም። የግብጽ ቤተ ክርስቲያን ጉዳይ አይደለም ብለን ግን በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ስር ኾነን ያሬዳዊ መዝሙር አያስፈልገንም ወይም በኦርጋንና በፒያኖ እንዘምር ማለት አንችልም። እነርሱ በያሬዳዊ መዝሙር ስላልዘመሩ ብለንም ሃይማኖታዊ (የዶግማ) ወይም የቀኖና ችግር አለባቸው አንልም፤ ውሳኔው በብሔራዊ ጉባኤ የተወሰነ ነውና።

ከብሔራውያን ጉባኤያት በተጨማሪ ሀገረ ስብከታዊ ጉባኤም ሊደረግ ይችላል። አጥቢያዊ ጉባኤም ሊኖር ይችላል። ነገር ግን በአንድ ሀገረ ስብከት የተወሰነው ውሳኔ በሌላ ሀገረ ስብከት ተፈጻሚ ላይኾን ይችላል። በአንድ አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን የሚሠራ ቀኖናም በሌላ አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ላይሠራ ይችላል። በኢትዮጵያ ውስጥ በአንዳንድ ገዳማት ላይ ሴቶች አይገቡም የሚባለው የዚያ ገዳም ብቻ ቀኖና ስለሚኾን ነው።

## ***<u>መ) የቅዱሳን አበው ቀኖናት</u>***

እነዚኽ ቀኖናት ምንም እንኳን በግለሰብ ደረጃ የተወሰኑ ቢኾኑም ቤተ ክርስቲያን የእኔ ብላ የተቀበለቻቸው ቀኖናት ናቸው። ለምሳሌ ሥርዓተ ምንኩስና የነ አባ እንጦንስ ወይም የእነ አባ ጳኩሚስ ሃይማኖት አይደለም፤ የእነዚህ ቅዱሳን አባቶች የትሩፋት ሥራ እንጂ። አባ ጊዮርጊስ ዘጋሥጫ ስለ ቅዱስ ቁርባን የተናገረው ሥርዓት የኢ/ኦ/ተ/ቤ/ክ/ ሥርዓት ኾኖ የቀረውም ከዚህ አንጻር ነው። የቅዱሳን ገድላትና ድርሳናትም እንደምንጭነት ይጠቀሳሉ።

## በቤተክርስቲያን የተለያዩ ቀኖናት ይገኛሉ

## ፩:- የቅዱሳት መጻሕፍት ቀኖና

የቅዱሳት መጻሕፍት ቀኖና ስንል የመጻሕፍቱ እውነተኛነትን፣ ቅዱስነትንና አምላካዊነትን የተመለከተ ማለታችን ነው። በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን ሰማኒያ አሃዱ(፹፩) መጻሕፍት በመጻሕፍ ቅዱስ እንቀበላለን።

፪:- የአጿማት ቀኖና ፡_በቤተክርስቲያን በዓመት ውስጥ 7 አጿማት አሉን። እነዚህም

ሀ) አቢይ ጾም

ለ) ጾመ ሐዋርያት

ሐ) የፍልሰታ ጾም

መ) የነቢያት ጾም

ሠ) ጾም ገሃድ

ረ) የነነዌ ጾም

ሰ) ዓርብና ረቡእ ናቸው፡፡

**፫:-የበዓላት ቀኖና፡**_በቤተክርስቲያን ዘጠኝ ዓበይት የጌታ በዓላትና ዘጠኝ ንዑሳን በዓላት አሉ።

**ዘጠኙ ዓበይት የጌታ በዓላት፡**

፩ኛ)ብስራት ፪ኛ)ልደት፣ ፫ኛ)ጥምቀት፣ ፬ኛ)ደብረታቦር፣ ፭ኛ)ሆሳዕና፣ ፮ኛ)ስቅለት፣፯ኛ)ትንሣኤ፣ ፰ኛ)እርገት እና ፱ኛ)ጰራቅሊጦስ ናቸው፡፡

**ዘጠኙ ንዑሳን የጌታ በዓላት፡**_

፩ኛ)መስቀል፣ ፪ኛ)ስብከት፣ ፫ኛ)ብርሃን፣ ፬ኛ)ኖላዊ፣ ፭ኛ)ግዝረት፣ ፮ኛ)ልደተ ስምዖን፣ ፯ኛ)ቃና ዘገሊላ፣ ፰ኛ)ደብረዘይት እና ፱ኛ)የመጋቢት መስቀል ናቸው።

፨ የእመቤታችን በዓላት ልደታ፣ በዓታ፣ ፍልሰታ፣ አስተርአዮ፣ በመቅድመ ተአምር የተጨመሩ ፴፫ቱ በዓላት ማርያም በየወሩ በ፳፩ የሚከበረው የእመቤታችን በዓል፣ በ፳፱ የሚከበረው በዓለ እግዚእ፣ በ፲፪ የሚከበረው የቅዱስ ሚካኤለ በዓል እና ሌሎችም በዓላት የተጨመሩት በዐፄ ዘርዐ ያዕቆብ ዘመነ መንግስት ነው። የህንን ስንክሳር መጽሐፍ በዝርዝር ያሳየናል። ይኸውም በየዓመቱ(በየዕለቱ)የሚከበረውን ቅዱስ ወይም ጻድቅ የሕይወት ታሪክ፣ አሟሟት በዝርዝር የያዘ መጽሐፍ ነው።(ምንጭ የኢ\ኦ\ተ\ቤ\ክርስቲያን ታሪክ በአባ ጎርጎሪዎስ 1991 ዓ. ም 3ኛ ዕትም ገጽ121)

፬:-የሥርዓተ አምልኮና የምስጢራተ ቤተክርስቲያን ቀኖና
በቤተ ክርስቲያን ውስጥ የምንፈጽመው ማንኛውም ዓይነት መንፈሳዊ ድርጊት የአምልኮ ባሕርይ አለው። ስናምን፣ ስንሰጥ፣ ስንቀበል ኹሉ አምልኮ ነው። ማንኛውንም ዓይነት ምሥጢር ስንፈጽም የእግዚአብሔር መኾናችንን ነው የምንገልጠው።

ያለ ሃይማኖት ሀብተ መንፈስ ቅዱስን መቀበል አይቻልም። የእግዚአብሔር ሀብት ከእግዚአብሔር ጋር በመኾን እንጂ እንደ ስምዖን መሠሪ የምንገዛው አይደለምና።
ሃይማኖት መታዘዝንም ይጨምራልና እንደ ቀኖና ዲያቆኑን፣ ቄሱን ወይም ጳጳሱን ማክበር ይጠበቅብናል። በጉድለት፣ በትዕቢት፣ በጭቅጭቅ የምንቀበል ከኾነ አለመታዘዝ ነው። ስለዚኽ ቀኖናና አምልኮ በእጅጉ የተቈራኙ መኾናቸውን ዐውቀን በቤተ ክርስቲያን ውስጥ በምንፈጽማቸው መንፈሳዊ ድርጊቶች ላይ ልንጠነቀቅ ይገባናል።

## ***፭:-የቅዱሳን ቀኖና***

ቅዱሳንን ማክበር የተጀመረው በኹለተኛው መቶ ክፍለ ዘመን ምእመናን ቀድመው ይታሰቡና ይከበሩ የነበሩት ቅዱሳን ሰማዕታት በማክበር ነበር። በ4ኛው መቶ ክፍለ ዘመን አንዳንድ ሰዎች በራሳቸው እይታ ቅዱስ እንደኾነ የሚያስቡትን ኹሉ ቅዱስ/ጻድቅ ለማስባል ስለተነሣሡ ቤተ ክርስቲያን በጉባኤ ቀኖና ቅዱሳንን ማውጣት ጀመረች። ይህም ማለት ግን ለሰዎቹ ቅድስናን ሰጠች ማለት ሳይኾን ለቅድስናቸው ዕውቅናን ሰጠች ለማለት ነው። ይኸውም ከትሩፋት ሥራቸው እንድንማር፣ በቃል ኪዳናቸው እንድንጠቀም፣ አሰረ ፍኖታቸውን እንድንከተል ነው።

አንድን ቅዱስ ቅዱስ ለማለት በሃይማኖትና በክርስቲያናዊ ሥነምግባራቸው በሚያደርጉት(ባደረጉት) ገቢረ ተአምራት (በአጸደ ሥጋና በአጸደ ነፍሥ) ለቤተክርስቲያን ባደረጉት ለየት ያለ አገልግሎት ለምሳሌ፡_ቅዱስ ላሊበላ፣ አቡነ ተክለሃይማኖት፣ አቡነ ገብረ መንፈስቅዱስ፣ አቡነ ጴጥሮስ የመሳሰሉትን ለኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ያደረጉትን አስተዋጽኦ ማስታወሱ በቂ ሊኾን ይችላል።

እንዲህ በቤተክርስቲያን ቀኖና መሰረት ቅዱስ የተባለ ጻድቅ በስሙ ቤተ ክርስቲያን ይታነጽለታል፤
ገድል ይጻፍለታል፤ በዓል ይደረግለታል፤ ቅድስናውን አጕልቶ የሚያሳይ ሥዕል ይሣልለታል፤ ዐፅሙ በክብር እንዲያርፍና ምእመናን እንዲያከብሩት ይደረጋል፤ ምእመናን በስሙ ሊሰየሙና ውሉደ እግዚአብሔር ሊባሉ ይችላሉ (በዓላት ምን፡ ለምን፡ እንዴት፡፣ በዲ፡፡ን ብርሃኑ አድማስ፣ ፪፻፰ ዓ።ም።፣ ገጽ ፩፬፬፡፩፬፰)፡

## ***ትውፊት***

**ትውፊት** አወፈየ፣አወረሰ ከሚለው የግዕዝ ቃል የወጣ ስም በመሆኑ ትርጓሜውም ውርስ፣ቅብብል ማለት ነው ።

ይኸውም አንድ ትውልድ (ሰው)ከእርሱ በፊት ከነበሩት የሚወርሰው፣የሚያገኘው፣የሚቀበለው ነገር ነው ሂደቱም በዚህ የሚያበቃ ሳይሆን እርሱም በተራው ለተተኪው ያስተላልፋል። *ያለ ትውፊት ስለ ቤተክርስቲያን ስርአት ቀርቶ በትውፊት የማያምኑት "ክርስትያን" ነን ባዮች ስለሚቀበሉትም ወንጌል መነጋገር አይቻልም ።

*በክርስትና አለም ጌታችን ካስተማራቸእ ሰርቶ ካሳያቸው ሑሩ ወመሀሩ ብሎ ካዘዛቸው ሐዋርያት ደቀመዛሙርቶቻቸው ብዙ ነገር ወርሰዋል።እነዚህ ደቀመዛሙርቶቻቸውም ሐዋርያን አበው ለመባል የበቁት ሐዋርያትን መስለው ሆነውም በመገኘታቸው ነው ።

*ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ በእግሩ ለተተካው ለመንፈስ ቅዱስ ልጁ ለጢሞቲዎስ በላከው መልእክት "አንተ ግን ትምህርቴን እና አካሄዴን ፣አሳቤንም፣ እምነቴንም፣ትዕግስቴንም፣ፍቅሬንም፣መፅና ቴንም፣ስደቴንም፣መከራዬንን ተቀበልህ ፪ኛ ጢሞ 3:10-11 በማለት እንደመሰከረለት በክርስትናው ጉዞ አባቶቹን የሚተካ ትውልድ ሁለመናቸውን ወርሶ መገኘት አለበት ያለበለዚያ ትውልድ ነው ተብሎ ሊቆጠር አይችልም የራሱን አመለካከት መንገድ እና ፍልስፍና ብቻ በመከተል አዲስ መሰረት እጥላለሁ ባይ ስለሚሆን ከጥንት ሲተላለፍ የነበረው መንፈሳዊ ቅብብሎሽ በእርሱ ዘመን ይገደበታል ክርስትና ደግሞ ምንጩም ወንዙም አንድ ነው ።

አንድ ህዝብ የሆነ ባህል እንዳለው ይታወቃል ይህ ባህል የሚባለው ነገር ደግሞ የአመጋገብ፣የአለባበስ፣የእናናር እና የአምልኮ ስርዓትንም የሚያጠቃልል ነው ።

***<u>ለምሳሌ;</u>*** ኢትዮጵያዊ ልዩ ባህል የሚባለው ከኦሪት የተቀበልነው የአመጋገብ እና የአናናር ስርዓት ነው በተለይም ደግሞ አለባበሳችን (ክርስቲያናዊ)ስንመለከተው መፅሐፍ ቅዱሳዊ

ማስረጃ ቢኖረውም ለእኛ ለመድረስ ያበቃው ግን ቅብብሎ(ትውፊቱ ነው ።ስለዚህ በዝርዝር ያልተቀመጡ ነገሮችን(ሥርዓቶችን) በትክክል እንድንቀበላቸው የሚያደርገን ትውፊት ነው ።

# *ትውፊት እና እድገት*

ብዙ ሰዎች ሁል ግዜ የቀደሙትን ከተመለከትን ዕድገታችን የትውልዱም የፈጠራ ችሎታ ይቃረጣል ብለው ስጋታቸውን ይገልጣሉ ነገር ግን ትውፊት እድገትን እይገድብም እንዲያውም ዕድገቱ የተስተካከለ እንዲሆን ያደርገዋል።ማደግ ማለት የራስን ቶ የሌላውን ብቻ መቀበል አይደለም የራስ የሆነን በአግባቡ መጠቀም እንጂ። በመጀመርያው መቶ ክፍለዘመን የነበሩ ቀደምት አበው የቤተክርስቲያንን አሰራር የአምልኮ ሥርአቱን ፣ልብሰተክህኖውን፣ጽንህውን፣ዕጣኑን፣መንበሩን ወዘተ.....ከኦሪታ ቤተመቅደስ ለቤተክርስቲያን እንደሚገባ አድርገው ተረከቡ እንጂ በዘመኑ ሰልጥኖ የነበረውን የግሪካዊ-ሮማ ፍልስፍናን አልጨመሩበትም ይህም የሆነው ስልጣኔው ፍልስፍናው ዕውቀቱ ሳይገባቸው ቀርቶ ሳይሆን የዚህ ስጋዊ ፍልስፍና እግዚአብሔርን መካድ ሥጋዊ ፍላጎትን ማርካት ምድራዊ ድሎትን ማደላደል መሆኑን ስለተገነዘቡ ነው ።

ይሁን እንጂ አባቶቻችን በዚያን ዘመን ክርስትናን ለማስፋፋት የሚያስችሉ ከቤተክርስቲያን ሥርአትና ትውፊት ጋር እማይጋጩ ያሉትንም ሀብት የማያጠፉ ጥበባትን ተጠቅመውባቸዋል።

***ለምሳሌ:*** ሰዓሊያን ስዕልፕ ቅዱሳንን ሲስሉ ቤተክርስቲያን በቃል እና በፅሁፍ ያቆየችውን መሰረት አድርገው ገለጡት እንጂ የራሳቸውን አመለካከት እና ፍላጎት ተጠቅመው ልብወለድ ስዕል አላቀረቡም።

# ***ትውፊት እና አፈታሪክ***

በእንዳንድ ምሁራን ዘንድ ትውፊትን ከአፈታሪክ ጋር መቀላቀሉ እየተለመደ ሄዶአል ሁለቱ ግን የሰማይ እና የምድር ያህል ይራራቃሉ።

***አፈታሪክ:-*** ሕዝቡን በአንድ ወቅት ስለተደረገ ነገር ጨምሮም ሆነ ቀንሶ ያለበለዝያም በልዩልዩ ምክንያት በጠፋው ነገር ላይ የራሱን አመለካከት ተክቶ የሚተርከው በጽሑፍ ያልሰፈርፕ በቃል ብቻ የሚወራ ታሪክ ብቻ ነው ።

***ትውፊት:-*** ግን የእዚህ አፈታሪክ ባለቤቶች የሆነውን ሕዝብ የምንለየው በትውፊት ነው ምክንያቱም ለእኛ" እነ እገሌ አሉ" ተብሎ የሚተረክልን ከአያት ከቅድመ አያት የተወረሰውን መሠረት በማድረግ ነውና ራሳቸው አፈታሪኮች ለዛቸው፣ቃናቸው፣ሥነጽሑፋዊ ውበታቸው ተጠብቆ ከትውልድ ወደ ትውልድ የሚተላለፉበት መንገድ በትውፊት ብቻ ነው ።

በትውፊት አማካኝነት አፈታሪኮች፣ተረቶች፣አባባሎች እን ሥነ ቃሎች ወደ ተከታዩ ትውልድ ይተላለፋሉ ክርስቲያናዊ ትውፊት ደግሞ ከነዚህ ሁሉ ይበልጣል ያለፉትን አበው መንፈሳዊ ኑሮ ፣ባህል፣ሥርዓት፣ታሪክ እና ገድል ያቆየናል እኛም ክርስትናን ተቀባዮች እንጂ ጀማሪዎች አይደለንምና ተቀብለን አባቶቻችን እንመስልበታለን።

# ***ክርስትያናዊ ትውፊት በዓለም መድረክ***

እስከ 451 ዓ.ም የቤተ-ክርስቲያን መለያየት ድረስ በቤተክርስቲያን የነበረው ክርስቲያናዊ ትውፊት አንድ ወጥ የነበረ በመሆኑ እስከዚህ ዘመን የነበሩ ቅዱሳን አበው በመላው አለም ጥንታውያን አብያተ ክርስትያናት በዓላቸው የሚከበረው አንድ ወጥ ነበር። ነገር ግን በአምስተኛው ክፍለ ዘመን በሮማ ቤተክርስቲያን መሪዎች የስልጣን ጥማት የተነሳ ቤተክርስቲያን ስትከፋፈል ከግሪክ ጀምሮ ወደ ምዕራብ የነበሩት ምዕራባውያን ሲባሉ ከዚያ

መልስ ያሉት ደግሞ ምስራቃውያን ተባሉ።ምስራቃውያኑ የአባቶቻቸውን ትውፊት በመጠበቃቸው ከምዕራባውያን ጋር ተጣሉ።ምዕራባውያኑ ደግሞ በዘመናቸው ከነበሩት የሮማ ነገስታት ጋር የመቀራረቡን ዕድል ተጠቅመው ቤተክርስቲያናቸውን ታላቅ ያደረጉ መስላቸው በስጋዊ ድሎት እና ፍልስፍና በመመራት ከእውነተኛው ትውፊት እርቀዋል።

## *የምዕራባውያን ትውፊት*

እስከ ፩ ኛው መቶ ክፍለ ዘመን ድረስ የነበረው ትውፊታቸው ከምሥራቅ ቤተክርስቲያን ጋር ተመሳሳይ ነበረ ለማለት ይቻላል ከዚህም የተነሳ ከምስራቃውያኑ ጋር የሚያመሳስላቸው ጥቂት ነገሮች ዛሬም ይገኛሉ:

***ለምሳሌ*** - በዓላተ ቅዱሳን -የእጽዋማትና ቀኖና - የገዳማት ሥርዓት

- ምሥጢረ ቤተክርስቲያን - የቅዱሳን አማላጅነት ወዘተ......

ምዕራባውያኑ በ ኛው ክፍለ ዘመን ማርቲን ሉተር እና ተከታዬቹባስነሱት ተቃውሞ የተነሳ ብዙ የአበው ትውፊቶችን ለሥልጣኔ እያሉ ሲተዉ ምሥርቃውያኑ ግን ምንም ባይመቻቸውባይደላቸውና መንገዱ ሁሉ የሰማዕትነት ጉዞ ቢሆንባቸውም ማነታቸውን አልዘነጉም።

## *ትውፊት እና ቤተክርስቲያን*

ቤተክርስቲያን ስለ ክርስቲያናዊ ትውፊት ታላቅ ቦታ ትሰጣለች ጥንታዊ በመሆናም ከቀደምት አበው የወረሰችው አያሌ ነገር አላት። እነርሱም ሁለት ዓይነት ናቸው::

፩.የሚዳሰሱ:መጻህፍት፣ንዋያተቅድሳት፣አልባሳት፣አብያተ ክርስቲያናት፣ገዳማት፣አድባራት ወዘተ.....የዚህ ክፍል ናቸው።

፪. የማይዳሰሱ(የሚታዩና የሚሰሙ) ትውልዱከአባቶች በመስማት እና በማየት ለኑሮው የሚጠቀምባቸው ነገሮች ናቸው።

ስለዚህ ሁለቱ ሀብቶቻ ከትውልድ ወደ ትውልድ የሚተላለፉት የቤተክርስቲያን መሆናቸውም የሚረጋገጠው በትውፊት ነው ።

## ***ትውፊት እና ቅዱሳት መጻህፍት***

ትውፊት ከቅዱሳን መጻህፍት ጋር የሚጋጭ የሚመስላቸው ብዙ ሰዎች አሉ ነገር ግን ደም ከደም ስር ጋር እንደማይጋጭ ሁሉ እነርሱም አይጋጩም ምክንያቱም;

- ትውፊት መጽሀፍ ቅዱስን ያገኘንበት መንገድ ነው አበው መጽሀፍ ቅዱስ ይሄ ነው ብለው ባያስረክቡን ኖሮ ይህ ትውልድስ በምን ያውቀው ነበር? በመሆኑም መጽሀፍ ቅዱስን ለማግኘት የቻልነው አበው ስላቆዩን ቤተክርስቲያንም ስላረጋገጠችልን ነው ።

- ትውፊት የቅዱሳት መጻህፍት ቃል እንዳይፋለስ ይጠብቃል አበው መጻህፍትን ሲያስረክቡን የደራሲውን ገድልን የተፃፈበትን ባህል የመጻህፍቱን ትርጋሜ ከምንጩ የቀዱትን ጭምር ነው ይህም ማንም በየትም ዘመን ተነስቶ የራሱን ሀሳብ እና ፍልስፍና በመጨመር የቅዱሳት መጻህፍትን ቃል እንዳያጣምም አድርጎታል ።

- ትውፊት ቅዱሳት መጻህፍትን ያብራራል።

## ***ትውፊትን መጠበቅ***

ባለንበት ዘመን ብዙ ሰዎች አንድ ጥያቄ ሲጠይቁ ይሰማል።(የእምነት ድርጅቶች ለምን በዙ?) ለዚህ ጥያቄ መልሱ  አንድ ብቻ ነው (ሐዋርያዊ ትውፊት በመጣሱ) የሚለው ነው አባቶቻችን ማናቸውንም  አይነት ነገር የሚፈፅሙት አባቶቻቸውን ተመልክተው ከእነርሱ ተረድተው ከስርዓታቸው እና ከሀይማኖታቸው ከትምህርቶቻቸው እና ከመንገዳቸው ሳይወጡ ነው በዚህም የተነሳ አባቶቻቸውን መስለው አባቶቻቸውንም ሆነው ይገዙ ነበር።

የእነዚህ አበው ትውፊት እየተረሳ እና እየተናቀ መምጣት ደግሞ በመንፈሳዊ ኑሮ ዙሪያ ታጥሮ የነበረውን እና የክህደት ትምሕርት ወደ ቤተክርስቲያን እንዳይገባ  የብረት ግንብ ሆኖበት የኖረውን አጥር አፈረሰው። የሰው ልጅ እግዚአብሔርን እየለቀቀ በገዛ ምኞቱ ሲንዝ ቤተክርስቲያናችን ግን አስቀድማ ከአበው ከሐዋርያት እና አስረፍኖታቸውን ተከትለው ከተነሱ ቅዱሳን ያገኘችውን ርቱዕ የሆነ እሱም ሳትከልስ፣ሳትበርዝ፣ሳትጥል እና ሳትነጥል ይዛ መገኘታ ምን ያህል ሐዋርያዊት ፣ርትዕት ቅድስት ንፅህት እንደሆነች ይገልጥልናል።

በመሆኑም የቤተክርስቲያን ትውፊት ተጠብቆ መገኘት ብሎም በየጊዜውም ትምሕርት መስጠት አስፈላጊ ነው።

Basic HTML view

o)

# ትውፊት

ትውፊት አንጋፋ የሃይማኖት መመሪያ ከመሆኑ ባሻገር ያለ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ያልተጻፈ ታሪኩን ከትውልድ ትውልድ የደረሰበት መንገድ ነው።

ከ1486 ዘመን በፊት የተጻፈ ህግ አልነበረም በዚያን ጊዜ የነበሩት አበው ይመሩ የነበሩት ሙሉ በሙሉ በትውፊት ወይም በህገ ልቡና ነበር ማለት ነው።

ወንጌልን በመላው ዓለም እንዲያስተምሩ የተላኩት የጌታ ደቀመዛሙርቱ ሁሉም ሲሆኑ በሃያ ሰባቱ በሓዲስ ኪዳን መጻሕፍት ላይ ግን የምናገኘው የአምስቱን ሐዋሪያት ብቻ ነው። የእነርሱም ቢሆን ሙሉ ትምህርታቸው በጽሁፍ አልተጻፈም።

የቀሩትሐዋሪያትስበዚህም መሰረት የቀሩት ሐዋሪያት ያስተማሩት፣ የሰበኩት፣ አሁን ለዚህ ትውልድ የደረሰው በትውፊት መሆኑ የታወቀ ነው።

<እንድጽፍላችሁ የምፈልገው ብዙ ነገር ሳለኝ በወረቀትና በቀለም ልጽፈው አልወድም ዳሩ ግን ደስታችሁ ፍጹም እንዲሆን ወደ እናንተም ልመጣ አፍ ለአፍም ልናገራችሁ ተስፋ አደርጋለሁ።>> ፪ኛ ዮሐ ፩÷፲፪ ይህ ማለት ዮሐንስ በቃል ያስተማራቸው እስካሁን ለኛ የደረሰውን የምንጠቀምበት ከአበው በትውፊት መልክ ከትውልድ ትውልድ እየተቀባበለ

የመጣ መሆኑን ልብ ልንል ይገባል።

በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን ትውፊት ትልቅ ቦታና ድርሻ አለው።

ሐዋሪያትና ትውፊታዊ መርጃ

ሐዋሪያት ወንጌልን ሲሰብኩ በጽሁፍ ያልሰፈሩ ዳሩ ግን በቃል ሲተረኩ የነበሩ ትውፊታዊ መረጃዎችን ይጠቅሱ እንደነበር መጽሐፍ ቅዱስ የሚያረጋግጠው ሀቅ ነው።

ለምሣሌ፡_ በጳውሎስ መልዕክት <<ኢያኔስና ኢያንበሬስም ሙሴን እንደተቃወሙት እንዲሁ እነዚህ ደግሞ አእምሮአቸው የጠፋባቸው ስለ እምነትም የተጣሉ ሰዎች ሆነው እውነትን ይቃወማሉ>> ፪ኛ ጢሞ፫÷፰በጳውሎስና በሙሴ ዘመን ያለው የዘመን ርቀት እጅግ በጣም ብዙ ሆኖ ሳለ ጳውሎስ ሙሴ በፈርኦን ፊት ተአምር ሲያደርግ እነርሱም ምትሐታዊ ተአምርን በማድረግ ሙሴን ይቃወሙት የነበሩትን የፈርኦን ጠንቋዮችና አስማተኞች ዘዳ፡ ፯÷፲፩_፲፫ ሥማቸው ሙሴ በጻፈው መጽሐፍ ላይ ሳይኖር እርሱ ግን ሥማቸውን ጠቅሶ መናገሩ በትውፊት ያገኘው መሆኑን የሚያሳይ ነው።

ትውፊታዊ መረጃን መቀበለ ሃይማኖታዊ ግደታ ነው። ፪ኛ ተሰሎ ፪÷፲፭ <እንግዲያስ ወንድሞች ሆይ ጸንታችሁ ቁሙ በቃላችንም ቢሆን ወይም በመልዕክታችን የተማራችሁትን ወግ ያዙ ሲል ትውፊትን ማለቱ እንደሆን የተረጋገጠ ነው። ይህ ትዕዛዝ ደግሞ ለተሰሎንቄ ሰዎች ብቻ ሳይሆን በእምነት ጳውሎስን ለምንመስል ሁሉ የተነገረ ነው።

የመጽሐፍ ቅዱስ ማስረጃዎችየቅዱስ ጳውሎስ መልዕክት

ለፊልጵ ፬÷፱ <ከእኔ የተማራችሁትንና የተቀበላችሁትን የሰማችሁትን ያያችሁትንም እነዚህን አድርጉ የሰላምም አምላክ ከናንተ ጋር ይሆናል።

በዘመነ አበው ይህ ዘመን ከአባታችን ከአዳም ጀምሮ እስከ ሙሴ ድረስ ያለው ነው በዚህ

ዘመን አበው በትውፊት እግዚአብሔርን የሚያውቁበትና በሕግ(ልቡናዊ)በአምልኮ ፈጣሪያቸውን ደስ ያሰኙበት ዘመን ነው።

፪ኛ ጢሞ ፫፥፲፮ (የእግዚአብሔር ሰው ፍጹምና ለበጎ ሥራ ሁሉ የተዘጋጀ ይሆን ዘንድ የእግዚአብሔር መነፈስ ያለበት መጽሐፍ ሁሉ ለትምህርትና ለተግሳጽ ልብንም ለማቅናት በጽድቅም ላለው ምክር ደግሞ ይጠቅማል።

ጳውሎስ 66ቱ መጸሐፍ ቅዱስ ብቻ ለጽድቅ ይጠቅማል አላለም ሌሎችም በእግዚአብሔር መንፈስ የተጻፉትን ቅዱሳት መጻሕፍት የሕይወታችን መመሪያ እናደርግ ዘንድ መክሮናል። ምክሩም ጠቃሚና አስፈላጊ መሆኑን ኦርቶዶክሳዊያን እናምናለን። ስለዚህም በቤተክርስቲያናችን ያሉትን የእግዚአብሔር መንፈስ ያለባቸውን ቅዱሳት መጻሕፍት ሁሉ ለክርስቲያናዊ ሕይወታችን እንገለገልባቸዋለን።

በኢ/ኦ/ተ/ቤክርስቲያን

***በሰሜን አሜሪካ በዋሽንግተን ዲሲ እና አካባቢው ሀገረ ስብከት***

***በ/ደ/ም/ቅ/ሚ/ካቴድራል እና የጽ/ጽ/ስ/ት/ቤት***